በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን
ETHIOPIAN CUSTOMS AUTHORITHY
የአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
ADDIS ABABA KALITY CUSTOMS BRANCH OFFICE
የውስጥ ማስታወሻ /INTER OFFICE MEMO/

ለ፡- ም/ሥራ አስኪያጅ /የጉምሩክ ጉዳዮች ዘርፍ/ ቁጥር፡ ሰ/አ/ጽ/ቤት 226/09
ለ፡- ም/ሥራ አስኪያጅ /ኮርፖሬትና ሞደርናይዜሽን ዘርፍ/
ለ፡- ጉምሩክ አቤቱታ አጣሪ ጽ/ቤት ቀን፡ 16/01/09 ዓ.ም
ለ፡- ጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈፃፀም የሥራ ሂደት
ለ፡- ድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት የሥራ ሂደት
ለ፡- ህግ ማስከበር የሥራ ሂደት
ለ፡- ደንበኞች አገልግሎት የሥራ ሂደት
ለ፡- መጋዘን አስተዳደርና ቁጥጥር የሥራ ሂደት
ከ፡- ሥራ አስኪያጅ ጽ/ቤት
አ/አ/ቃ/ጉ/ቅ/ጽ/ቤት፣

16/01/09

በቁጥር 3.0/560/09 በቀን 10/01/2009 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ወደ ሃገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎች ላይ የሚከሰቱ የዓይነት፣ የመጠን፣ የብዛት ወይም የስሪት አገር የአገላለጽ ልዩነቶች የተገኙበትን ዕቃ በአስተዳደራዊ ውሳኔ ስለመጨረስ ወይም በወንጀል እንዲታይ እንዲደረግ እያሳሰብኩ የተገለፀበትን ደብዳቤ 6 ገጽ ኮፒ በዚህ ሸኚ ደብዳቤ የተላከ መሆኑን አገልፃለሁ፡፡

ከሰላምታ ጋር

18/01/09

<u>ግልባጭ</u>፡-

- ለም/ሥራ አስኪያጅ ጽ/ቤት /የጉምሩክ ጉዳዮች/
- ለጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈፃፀም የሥራ ሂደት

<u>አ.አ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት</u>

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
ETHIOPIAN REVENUES AND CUSTOMS AUTHORITY

ቁጥር Ref. No 3-01560/09
ቀን Date 10 መስከ. 2009፣

የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ለሚፈፀምባቸው የኢ.ገ.ጉ.ባ.ቅ/ጽ/ቤቶች በሙሉ

በያሉበት

ጉዳዩ፡ የአገላለጽ ልዩነት የተገኘበትን ዕቃ በአስተዳደራዊ ውሳኔ ስለመጨረስ ወይም በወንጀል እንዲታይ ስለማድረግ

ወደ ሀገር ውስጥ ከሚገቡ ዕቃዎች ጋር ተያይዞ ከሞላ ጎደል በሁሉም የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች የአገላለጽ ልዩነት ያጋጥማል፡፡ ነገር ግን ቅ/ጽ/ቤቶቹ የአገላለጽ ልዩነት ባጋጠማቸው ጊዜ ጉዳዩን የሚያስተናግዱበት መንገድ ወጥነትና ተመሣሣይነት ያለው አይደለም፡፡ ይህ ደግሞ አሠራሩ የቅሬታና የመልካም አስተዳደር ችግር መንስኤ እንዲሆን አድርጐታል፡፡

ስለሆነም ቅ/ጽ/ቤቶቹ የገቢ ዕቃዎችን በሚያስተናግዱበት ጊዜ የሚያጋጥሟቸውን የአገላለጽ ልዩነቶች የሚያስተናግዱበት አሠራር ወጥና ተመሣሣይነት ያለው እንዲሆን ለማድረግ ህጉን መሠረት ያደረገና ግልጽነት ያለው የሥራ መመሪያ ማስተላለፍ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በዚሁ መሠረት የአገላለጽ ልዩነት ማለት ምን ማለት እንደሆነና አስተዳዳራዊ ቅጣትና የወንጀል ኃላፊነት የሚያስከትሉ የአገላለጽ ልዩነቶች የትኞቹ እንደሆኑ እንዲሁም አስተዳደራዊ ቅጣትም ሆነ የወንጀል ኃላፊነት የማያስከትሉ የአገላለጽ ልዩነቶች ምን ዓይነት ልዩነቶች እንደሆኑ ግልጽ ለማድረግና በገቢ ዕቃዎች ላይ አስተዳደራዊ ቅጣት ወይም የወንጀል ኃላፊነት የሚያስከትል የአገላለጽ ልዩነት በሚያጋጥምበት ጊዜ ቅ/ጽ/ቤቶች ሊከተሉት የሚገባቸውን ወጥ የሆነ የአሠራር ሥርዓት ለመዘርጋት ተሞክሯል፡፡



ስልክ ቁ / Tel.. 011 662 98 00
ፋክስ / Fax: 011 662 99 06
ኢሜል / Email: erca@ethionet.et
ድረ ገጽ / Website: www.erca.gov.et
ፖ.ሣ.ቁ / P.O.Box: 2559
አዲስ አበባ-ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia

...ለጽ ልዩነት የተነሳ ለሚወሰነው አስተዳደራዊ ቅጣት መሠረቱ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር ...9/2006 አንቀጽ 157 ሲሆን የወንጀል ኃላፊነት የሚያስከትለው ደግሞ አንቀጽ 169(2) ነው፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 157(1) መሠረት ለጉምሩክ ፎርማሊቲ በቀረበ የዕቃ ዲክላራሲዮን ላይ ያልተመዘገበ ወይም ትክክለኛ መግለጫ ያልተሰጠት (የተሳሳተ መግለጫ የተሰጠበት) ዕቃ ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት ወይም አነስተኛ ቀረጥና ታክስ ተከፍሎበት ወደ ሀገር እንዲገባ ወይም ከሀገር እንዲወጣ የተደረገ ወይም ለማድረግ የተሞከረ እንደሆነና በዲክላራሲዮኑ ላይ ያልተመዘገበው ወይም ትክክለኛ ያልሆነ መግለጫ የቀረበበት ዕቃ ዋጋ በዲክላራሲዮን በትክክል ከተገለፀው ዕቃ ጠቅላላ ዋጋ ጋር ሲነፃፀር ከ50% ያልበለጠ ሆኖ ከተገኘ በዲክላራሲዮን ባልተመዘገበው ወይም ትክክለኛ ያልሆነ መግለጫ በተሰጠበት ዕቃ ላይ ሊከፈል የሚገባው ቀረጥና ታክስ መከፈሉ እንደተጠበቀ ሆኖ የዚሁ ቀረጥና ታክስ እጥፍ በሆነ የገንዘብ መቀጮ እንደሚቀጣ ተደንግጓል፡፡

በዲክላራሲዮን ያልተመዘገበው ወይም ትክክለኛ መግለጫ ያልተሰጠበት ዕቃ ዋጋ በዲክላራሲዮን በትክክል ከተመዘገበው ዕቃ ጠቅላላ ዋጋ ጋር ሲነፃፀር ከ50% በላይ ሆኖ ከተገኘ ጉዳዩ በወንጀል የሚያስጠይቅ ሆኖ ዕቃው ወዲያውኑ እንዲወረስ ይደረጋል፡፡

ነገር ግን ይህን መመሪያ ለማስተላለፍ መነሻ የሆነውና በቅ/ጽ/ቤቶች መካከል ወጥነት የጐደለው አሠራር የሚታይበት ዋናውና መሠረታዊ ጉዳይ "ትክክለኛ መግለጫ ያልተሰጠበት ዕቃ" ማለት ምን ማለት ነው የሚለው ስለሆነ በዚህ ጉዳይ ላይ ግልጽነት መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ በተለምዶ የአገላለጽ ልዩነት የተገኘበት ዕቃ የምንለው ትክክለኛ መግለጫ ያልተሰጠበት ወይም በዲክላራሲዮን ያልተመዘገበ ዕቃ ለማለት ነው፡፡

የአገላለጽ ልዩነት አስተዳደራዊ ቅጣት ወይም የወንጀል ኃላፊነት ስለሚያስከትልበት ሁኔታ ከአዋጁ በተጨማሪ በመመሪያ ቁጥር 112/2008 ላይ በዝርዝር የተመለከተ ሲሆን ይህ መመሪያ የታሪፍና የዋጋ ትመና አሠራርን ከሚደነግገው መመሪያ ቁጥር 111/2008 የተለየ ነው፡፡

አስመጪው ወይም የጉምሩክ አስተላላፊው ከዕቃው ትክክለኛ ዋጋ ያነሰ ዋጋ ለጉምሩክ ቢያቀርብ ወይም ዕቃውን የመደበበት ታሪፍ ከትክክለኛው ታሪፍ ያነሰ ሆኖ ቢገኝ መመሪያ ቁጥር 111/2008 በአስመጪው /በጉምሩክ አስተላላፊው/ ላይ አስተዳደራዊ ቅጣትም ሆነ የወንጀል ኃላፊነትን አያስከትልም፡፡ ስለሆነም በዋጋ ወይም በታሪፍ አገላለጽ ላይ የሚታይ ስህተት ወይም ለጉምሩክ የቀረበ የተሳሳተ የዋጋ መግለጫ ወይም የታሪፍ አመዳደብ በአዋጁ አንቀጽ 157(1) የሚሸፈን አይሆንም፡፡

ኑም በአዋጁ አንቀጽ 157(1) "ትክክለኛ መግለጫ ያልተሰጠበት ዕቃ" ማለት የዕቃውን ዐይነት፣መጠን ብዛት ወይም የሥሪት ሀገር በሚመለከት ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥና ታክስ ሊያሳንስ ወይም ሊያስቀር በሚችል መልኩ ትክክለኛ ያልሆነና የተሳሳተ መግለጫ የቀረበበት ዕቃ ማለት ሲሆን የዋጋና የታሪፍ አገላለጽን የሚያካትት አይደለም፡፡

በአዋጁ አንቀጽ 2(49) የተተረጐመውና "በህጋዊ ዕቃ ከለላነት መጠቀም" የሚለው ሐረግ የዋጋ ልዩነትንም ጭምር የጠቀሰ ቢሆንም ሐረጉ የተተረጐመው በአዋጁ አንቀጽ 157(1) እና 169(2) ላይ በትክክል ተገልጾ ጥቅም ላይ እንዲውል ለማድረግ ታስቦ የነበረ ቢሆንም በእነዚህ ድንጋጌዎች ውስጥ ሳይጠቀስና ጥቅም ላይ ሳይውል የቀረ በመሆኑ በአንቀጽ 157 እና 169 አፈፃፀም ልንጠቀምበት አይገባም፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የዋጋና ታሪፍ ልዩነቶች በአንቀጽ 157 እና 169 መሠረት አስተዳደራዊ ቅጣትና የወንጀል ኃላፊነት ሊያስከትሉ በሚችሉበት መልኩ ህጉን መተርጐም በአዋጁ አንቀጽ 122 መሠረት የድህረ አወጣጥ ኦዲት ተፈፃሚ በሚሆንበት ጊዜ ዕቃው ከተለቀቀ በኋላና ከመለቀቁ በፊት በሚጣለው መቀጫ መካከል ልዩነት እንዲፈጠር የሚያደርግ በመሆኑ የዋጋና ታሪፍ ልዩነት በአንቀጽ 157 ወይም 169 መሠረት ሊስተናገዱ አይገባም፡፡

ከዚሁ ጋር ተያይዞ የአዋጁ አንቀጽ 122 ተፈፃሚ መሆን ያለበት በዋጋና በታሪፍ ልዩነት ምክንያት ሳይከፈል በቀረ የቀረጥና ታክስ ልዩነት ላይ ሲሆን የዕቃው ዓይነት፣መጠን፣ብዛት ወይም የሥሪት አገር አገላለጽ ትክክለኛ ባለመሆኑ ምክንያት የተፈጠረ የቀረጥና ታክስ ልዩነት በድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት በሚገኝበት ጊዜ ተፈፃሚ መሆን ያለባቸው እንደሁኔታው የአዋጁ አንቀጽ 157 ወይም 169 ሊሆኑ ይገባል፡፡ ይህ የሚሆነው የአዋጁን አንቀጽ 121(3) ድንጋጌ ታሳቢ በማድረግ ነው፡፡

ስለሆነም በአገላለጽ ልዩነት ምክንያት በአዋጁ አንቀጽ 157(1) ወይም 169(2) መሠረት አስተዳደራዊ ቅጣት ለመወሰን ወይም ጉዳዩን ወደ ወንጀል ምርመራ ለመምራት የአገላለጽ ልዩነት የተከሰተው በዕቃው ዓይነት፣መጠን፣ብዛት ወይም የሥሪት አገር ላይ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ በዚህ መሠረት በመመሪያ ቁጥር 112/2008 እና በአዋጁ አንቀጽ 157 ወይም 169 መሠረት ህጋዊ እርምጃ ለመውሰድ ቅ/ጽ/ቤቶች የሚከተሉት መሟላታቸውን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡

1. የአገላለጽ ልዩነት የተከሰተው ወይም ትክክለኛ ያልሆነ መግለጫ የቀረበው በዕቃው ዓይነት፣መጠን፣ብዛት ወይም የሥሪት አገር ላይ መሆኑን፡፡
2. የአገላለጽ ልዩነቱ መከፈል የሚገባውን ቀረጥና ታክስ እንዳይከፈል የሚያደርግ ወይም መከፈል ከሚገባው ያነሰ ቀረጥና ታክስ እንዲወሰን የሚያደርግ መሆኑን፡፡

በሌላ በኩል የአገላለጽ ልዩነት የተከሰተው በዋጋና በታሪፍ አመዳደብ ላይ መሆኑ ከተረጋገጠ ትክክለኛውን ዋጋና ታሪፍ መሠረት በማድረግ ቀረጥና ታክሱን ወስኖ ከማሳወቅ በዘለለ አስመጪው /የጉምሩክ አስተላለፊው/ ለተጨማሪ ቅጣትና የወንጀል ኃላፊነት የሚዳረጉበት የህግ መሠረት አለመኖሩ መታወቅ ይኖርበታል፡፡

እንደዚሁም በአዋጁ አንቀጽ 157(1) እና 169(2) አፈፃፀም በአንቀጽ 169(2) “በዲክላራሲዮን ላይ ከተገለፀው ጠቅላላ ዋጋ 50% በላይ ሆኖ ከተገኘ” የሚለው ሐረግ “በዲክላራሲዮን ላይ ከተገለፀው ዕቃ ጠቅላላ ዋጋ 50% በላይ ሆኖ ከተገኘ” በሚል እንዲነበብና የዋጋና የታሪፍ አገላለጽ ልዩነቶች ከዕቃው ዓይነት፣መጠን፣ብዛት ወይም የሥሪት አገር አገላለጽ ልዩነቶች ጋር ተቀላቅለው በሚገኙበት ጊዜ ቅ/ጽ/ቤቶች በቅድሚያ የዕቃውን ዋጋ በመወሰንና ዕቃውን በትክክለኛው ታሪፍ ላይ በመመደብ ቀረጥና ታክሱን ወስኖ በዕቃው ዓይነት፣መጠን፣ብዛት ወይም የሥሪት አገር ላይ ለተፈፀመው የአገላለጽ ልዩነት ደግሞ በቀጣይነት አግባብነት ያለውን ውሳኔ መወሰን ይኖርባቸዋል፡፡

በመጨረሻም በዓይነት፣በመጠን፣በብዛት ወይም በስሪት አገር አገላለጽ ትክክለኛ ያልሆነ መግለጫ የቀረበበት ዕቃ ዋጋ በዲክላራሲዮን በትክክል ከተገለፀው ዕቃ ዋጋ ጋር ለማነፃፀር ቅ/ጽ/ቤቱ በቅድሚያ አስመጪው ወይም የጉምሩክ አስተላለፊው ባቀረበው ትክክለኛ ያልሆነ መግለጫ መሠረት ሊወሰን ይችል በነበረው ዋጋ እና ትክክለኛው የዕቃው ዓይነት፣መጠን፣ብዛት ወይም የሥሪት አገር ተወስዶ በሚወሰነው ትክክለኛ ዋጋ መካከል ያለውን ልዩነት ከወሰነ በኋላ በዲክላራሲዮን ከተገለፀው ዕቃ ጠቅላላ ዋጋ ጋር የሚያነጻጽረው ይህንኑ ልዩነት መሆን ይኖርበታል፡፡ ምክንያቱም አስመጪው ወይም ዲክላራሲዮን አቅራቢው እንዳጭበረበረ የሚቆጠረው ዲክሌር ሳያደርግ በደበቀው ዋጋ ልክ ስለሆነ ባቀረበው አሳሳች መግለጫ መሠረት የሚወሰነው የዋጋ ልክ ከንጽጽሩ ውጪ መሆን ይኖርበታል፡፡

ስለሆነም ሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች በገቢ ዕቃዎች ላይ የሚከሰቱ የዓይነት፣የመጠን የብዛት ወይም የሥሪት አገር የአገላለጽ ልዩነቶች ሲያጋጥሟቸው በዚህ መሠረት እንዲያስተናግዱ እየገለጽኩ በአፈፃፀም ሂደት የሚከሰቱ ችግሮች ወይም በመመሪያው ይዘት ላይ ግልጽ ያልሆኑ ሁኔታዎች ቢያጋጥሙ በጽሁፍ ሪፖርት እንዲደረግልን አሳስባለሁ።

ከሠላምታ ጋር




አብርሃም ንጉሴ
ም/ዋና ዳይሬክተር

<u>ግልባጭ</u>

- ለዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት
- ለህግ ማስከበር ሥራዎች ዘርፍ
- ለጉምሩክ ፕሮግራም ልማትና ድጋፍ ሥራዎች ዘርፍ
- ለጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች ክትትልና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት

<u>ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን</u>

- ለአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  <u>አዲስ አበባ</u>
- ለሞጆ ገቢ.ዎችና ጉምሩክ /ቅ/ጽ/ቤት
  <u>ሞጆ</u>
- ለአዳማ ገቢ.ዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  <u>አዳማ</u>
- ለሚሌ ገቢ.ዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  <u>ሚሌ</u>
- ለጋላፊ ገቢ.ዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  <u>ጋላፊ</u>
- ለሐዋሳ ገቢ.ዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  <u>ሐዋሳ</u>
- ለኮምቦልቻ ገቢ.ዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  <u>ኮምቦልቻ</u>
- ለመቀሌ ገቢ.ዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  <u>መቀሌ</u>
- ለባህርዳር ገቢ.ዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  <u>ባህርዳር</u>
- ለጅግጅጋ ገቢ.ዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  <u>ጅግጅጋ</u>
- ለሞያሌ ገቢ.ዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  <u>ሞያሌ</u>
- ለድሬዳዋ ገቢ.ዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  <u>ድሬዳዋ</u>
- ለጅማ ገቢ.ዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  <u>ጅማ</u>